የትምክህትና የጥበት ጨኸቶችን ስንታገል...

ሠይፈ ደርቤ 02-26-16

የአገራችንን ህዝቦች ከዚያ የመበታተን አደጋና የተሳሳተ መንገድ የታደጋቸው የጠራ መስመርና ህዝባዊነት ነው፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ላለፉት 25 ዓመታት እንኳን እንዲህ ዓለም በሚመሰክርለት ሰላም፣ ልማትና እድገት ቀርቶ ያኔ በነበርንበትም አንፃር አገር ባልነበረን! እነዚህን ሁለት አስርት ስንጓዝ ግን መንገዱ አልጋ በአልጋ አልነበረም፤ እንቅፋት የሌለውም አልነበረም፤ ፈተና ያልተጋረጠበትም አልነበረም። ድርቅ ተፈታትኖናል፣ በአገር ውስጥ እዚህም እዚያም በህዝቦች ላይ ጅምላ ግድያ ሲፈፅሙ የነበሩ ፀረ ሰላሞችና አሸባሪዎች ተፈታትነውናል፤ ወራሪው የሻዕቢያ ጦር ያለ ፍላጎታችን ለግባንበት ጦርነት እልህ በሚያስጨርስ ሁኔታ ተፈታትኖናል፤ ምርጫ 97 ተከትሎ ወጣቱን ለጥፋት በተጠቀመ ሀይል ፈተናም ተጋርጦ በራሱ በወጣቱ ያው ፈተና መሸነፉም አይዘነጋም።

እኒህ ሂደቶችና ተግዳሮቶች ሁሉ የጉዞአችን ፈተናዎች ነበሩ፤ አንዳቸውም ግን አላሸነፉንም። ያልተሸነፍንበት ምክንያት እንደ አገርና እንደ ስርዓት ህዝባዊነትና የጠራ መስመር ስላለንና ስለነበረን ነው። ያኔ የድህነት ዘበኛውን ታግሎ ያሸነፈው ህዝባዊ መስመር የአሁኑ ዋና ጠላቱ ድህነት ነው ሲባል የድህነት ዘበኞች ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል ማለት አይደለም። በዋናነት አስተሳሰቡ ተሰብሯል፤ ግን የድህነቱ ቅጥረኛ ብዙ ኣያሰጋንም፤ ይልቁንም ይህ የጥፋት ሀይል ጆሮውን የሚሰጠው፣ ልቡን የሚያውሰው ሀይል የሚያገኘው ድህነት ተስፋ ያስቆረጠው ሀይል ሲኖር ነው። የመልካም አስተዳደር ችግር ለተስፋ መቁረጥ መነሻ ሊሆን ስለሚችልም የጥፋቱ ሀይል እንዲህ አይነት ቀዳዳዎች መፈለጉ ያለና የሚጠበቅ ነው።

ስለዚህም ከተስፋ መቁረጥ በተቃራኒ በሀገሩ ላይ እምነት የፈጠረው ወጣትና አጠቃላዩ ህዝብ ከትላንት ዛሬ እያሳደገውና እያጎለበተው በመጣው ልማት አቅም ፈጥሮ፣ ዴሞክራሲውን አጎልብቶና ሰላሙን አስፍቶ ህይወቱን የተሻለ እንዲያደርግ ተስፋ መቁረጥን የሚያስከትሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተፈጠረው መድረክ ራሱ ፋና ወጊ ሆኖ ሊታገላቸው ይገባል። በቀዳዳው ተጠቅመው የባሰ ጥፋትና ትርምስ ሊያሰፍኑ የተነሱ ፀለምተኞችንም ሊታገላቸው ግድ ይላል። እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ የግል

ጥቅማቸውንና የጥፋት አጀንዳቸውን መዳረሻ በሌለው ቅዠትና ህልም በብጥብጥና ትርምስ ለማሳካት የሚተጉ ሀይሎች ወጣቱን ሽፋን አድርገው ሲጠቀሙበት ተስተውሏል።

በነገራችን ላይ እነዚህ ሀይሎች በዚህ መልክ የት ድረስ እንጓዝ ይሆን ብለው እንዲጠይቁ አይጠበቅም፤ ከማንም ቀድመው የትም ድረስ እንደማይጓዙ ጠንቅቀው ያውቁታልና፤ ይልቁንም በዚህ ሂደት የት ድረስ እንጓዝ ይሆን ብሎ መጠየቅና በዚህ መልክ የተጓዙ አገሮች የት እንደደረሱም ለማወቅ መትጋት ያለበት የአገራችን ወጣት ነው።

ይህን ከመገንዘብ ባለፈ ግን ለፀረ ሰላሞች ዋሻና ምሽግ ባለመሆን፣ ወደ ኋላ እንዳይመልሱት፣ ጥቅሙንም ለአፍታ እንዳያስተጓጉለብት አቋም በመያዝ የምለወጠው ስሰራና አገሬ ስታድግ ነው ብሎ ወጣቱ በተግባር የአገሩ ልጅ መሆኑን ሊያሳያቸው ይገባል። ወጣቱ ይህን እስካደረገ ድረስ ላለፉት ሁለት አስርታት ይዞት የዘለቀው መስመርና ህዝባዊው ስርዓት ጅምሩ እንዲሳካ እንደሚያደርገው ጥርጥር የለም።

በሌላ በኩል የጥፋት ሀይሎች ኦሮሚያ ላይ ብለው ብለው አልሆን ሲላቸው ክልል ማሰስ ቀጥለዋል፤ በዚህ ሂደት እነዚህ ቡድኖች እያደረሱት ያለው ጥፋት መድረሻው ምንድን ነው የሚል ጠያቂ አዕምሮ ያሻናል።

በተለይ እናውቃለን የምንል፣ በፊደል መጫወት የሰርካችን የሆነ ግለሰብ ባለአቋሞች እውቀት ማለት ህዝብን ማወቅ ማለት እንደሆነ ሳንዘነጋ፣ እውቀት ማለት ህዝባዊነት መሆኑንም ፊፅሞ ሳንረሳ ለሰላማችን እንደየድርሻችን ማዋጣት ይኖርብናል።በቅርቡ በአንድ የምሁራን መድረክ ላይ፣ አንድ ጎምቱ ፖለቲከኛና ስትራቴጂስት፣ “ለምሁር ለምሁርማ ጥፋትን የዕለት ተዕለት አጀንዳ ያደረገው ብርሃኑ ነጋም ምሁር ነው። ዋናው ነገር ህዝባዊነት ነው” ብለው ነበር። እንመለስ... ሰሞኑን የቅማንት ጉዳይን አጀንዳ አድርገው አልሳካ ያላቸው የጥፋት ሀይሎች የ”ፀ” እና “ጠ” ኳሶች ፈጥረው ከወዲህ ወዲያ ነገር እየጠለዙ ወልቃይትን መዳረሻ አድርገዋል። የወልቃይት ጉዳይ የማንነት ነው፣ የመሬት ነው በሚሉ ውስጣዊና ህዝባዊ መቆርቆር በሌላቸው የጅብ ፖለቲከኝነት አቋም መቆራረስና መነጣጠልን ለማወጅ አጀንዳ አልባ ስራ ፈቶች አጀንዳ ይሰጡ ጀምረዋል።

እኒህ ነጂው ሁላ የሚነዳቸው፣ ጋላቢው ሁላ የሚጋልባቸው በሁሉም ቦታ ከላይ ከላይ ያሉ፣ ከውስጥ ግን የሌሉ ግለሰብም፣ ተጠጋኒ አስረጅ ተነታራኪዎችና መርህ አልባዎች

በሚሰጡት ትንታኔ ከወዲህ ወዲያ መንገላታት አያሻም። ህዝባዊው ግንባር ኢህአዴግ ለዚህ መላ ነበረው፤ መላም አለው፣ መላም ይኖረዋል። በዚህ ረገድ ተረጋግቶ የተጀመረውን ልማትና ዴሞክራሲ እንደየሰልፋችንና ስምሪታችን ማስቀጠል ነው።

በሚቀጥሉት 30 ዓመታት ህዝቦች ይጠቅመናል፣ ይበጀናል ብለው የጋራ በሚያደርጉት አቋም ላይ ደርሰው እየተከራከሩና በሃሳብ እየተሟገቱ እንዲሄዱ የሚያስችላቸው ዛሬ የጀመርነውና እያሰፋነው ያለው መስመር በሁሉም ሰው ውስጥ እስኪጋባ ድረስ ኮሽታው ሊያስደነግጠን አይገባም። ኮሽታው እንዳይሰፋ ግን ውግንናችን ህዝብ ከመረጠው፣ መርጦም ትልቁን አደራና ኃላፊነት ካሸከመው ህዝባዊ ድርጅት ጋር ሊሆን ይገባል። እያንዳንዳችን ራሳችንን መመዘን የሚኖርብንም ኮሽታውን በምን ያክል ቀነስነው በሚል እንጂ ኮሽታውን በማስፋት ሊሆን አይገባም። ከዚህ በዘለለ የሚተነትን፣ ሃሳብ የሚበትንና አቅጣጫ የሚሰጥ የራሱ እንጂ የማንም አይደለም፤ በዚህ ረገድ የሚፈጠር የመርህ ስህተትም ከታጋይነትና ከመቆርቆር አለያም ከህዝባዊነት የሚመነጭ ሳይሆን የግለሰብና የግል ፍላጎትና አጀንዳ ነው፤

በዚህ ረገድ እጅግ ግራና ቀኝ ፅንፍ ላይ የቆመው የትምክህትና የጥበት ሀይል ጅብኛ የሆነና መድረሻውን በትርምስ የሚቋጭ አጀንዳ ይዞ ለማባላት የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ በተለይ ባለፉት ሳምንታት ውስጥ መገንዘብ ችለናል። በተለይ በየማህበራዊ ድረ ገፅ የጥፋት መንገደኛ የቀረፀውን አጀንዳ እንደ ፅንፈኛው ሁሉ ግራና ቀኝ እየተጓተትን በየፈንታችን በመርህ ላይ ተመስርተን ሳይሆን በስሜታችን የምንላጋውን ማየት ያሳዝናል። ህዝቡ የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ገብቶት ህገመንግስታዊ ጥያቄ ሲያነሳ፣ ይህን አድንቀን ጥያቄውን ለጥፋት እየተጠቀመበት ያለውን ሀይል ኮንነን፣ ህዝቡ ያነሳው ጥያቄ ግን መልስ ማግኘት አለበት ብለን መደምደምና ፀረ ሰላሙን ሀይል ማጋለጥና መታገል ሲገባን፣ የጥፋት ቡድኑ በሚሰጠው አጀንዳና የቁማር ጨዋታ ውስጥ ጠጠር ሆነን ከወዲህ ወዲያ መወራወራችንና መላጋታችን ተገቢ አይሆንም።

መንግስት ወይም መንግስትን ወይም ክልልን እየመራ ያለ ፓርቲ በዚህ ረገድ ለተነሳው ጥያቄ ቀድሞውኑ የመረጠው ህዝብ ሊጠይቀው መብቱ ነውና፣ ተጠሪነቱም ለህዝብ ነውና (በሌላ አነጋገር ህዝባዊ መንግስት ነውና) ጥያቄውን አዳምጦ መልስ መስጠቱ የሁልጊዜም ባህሪው ነው፤ ይልቅ ይህን አላግባብ በመለጠጥና በመተርጎም ቁማሩን ለሚጫወተው አካል ጠጠር እንዳንሆን ብንተጋ ችግሩን ለመቅረፍ፣ የተጀመረውን ልማትም ይበልጥ ለማስቀጠል

ያግዘናል።

የሃሳብ ትግል ነፃ ሆኖ መንሸራሸር ቢኖርበትም ቀድመን አቋም ይዘን የምንከራከርበትና ሌሎች አቋም እንዲይዙ የምናደርግበት ጉዳይ ልናፀናው ከምንሻው ዘላቂው ሰላማችን፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲያችንና ቀጣይነት ያለው ልማትና ልንደርስበት ከምንሻው አንድ የኢኮኖሚ ፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታ አኳያ ምን ያህል ይጠቅማል የሚለው ሊሆን ይገባል። የትኛውም ሀሳብ በበቀልና የተወሰኑ ወገኖችን በማስከፋት ላይ ተመስርቶ የሚሰነዘር ከሆነ ትርፍ የለውም፤ አትራፊውም አይታወቅም።

ምናልባት በዚህ አይነቱ እሰጥ አገባ ከሚፈጠር ማብቂያ የለሽ ንትርክ የጅብ ፖለቲከኞች “ውሻ በቀደደው…” እንዲሉ አበው፣ እንዳሻቸው እንዲንጡንና በመበጣበጣችን እንዲረኩ እድል ካልሰጠንና መጨረሻ ላይ እርስ በእርስ እንደጅቦቹ መበላላት ካልሆነ በቀር?! ልዩ ልዩ አስተሳሰብና ፍላጎት ያላቸው ህዝቦች ባሉባት አገር የሚያስማማው የተስማሙበት የጋራ ጉዳይ ነው፤ ያልተስማሙበት ጉዳይ ላይም ባለመስማማት ሊስማሙ የሚችሉት ይህን በሚያቻችለው የጋራ ጉዳያቸው ነው፤ እንደ እኛ አገር ብዝሃነት ሁሉም ህዝቦች የሚስማሙበት በፌዴራላዊ ህገመንግስቱ ነው።

የምንመዛቸው ሰበዞችም ከሃሳብ ነፃነት በስቲያ እነዚህ ፍላጎቶች ያሏቸውን ህዝቦች፣ ቡድኖችና አስተሳሰቦች ምን ያህል ያከብራሉ መባል አለበት። አንዱ ወገን ሲያጠፋ በምላሹ ጥፋትን የሚመልስ አስተሳሰብ፣ ወይ ትምክህተኝነት አለያም ጠባብነት የሚታይበት ነው።

ሃሳብን ሙጥኝ ብለው በምክንያታዊነት የሚከራከሩ ወገኖች ምላሻቸው ሰላማዊ ነው፣ የሀሳባቸው ውስጥ ንትርክ የለውም፣ ጥላቻና ቡድንተኝነትን አይሰብክም፤ ስለራሱ ሲከላከል ሌላውን ወቅሶና አንተ ቤት ጅብ አለ ብሎ ነገር አይጎነጉንም፤ ሁላችንም በጋራ ማየት አለብን ብሎ በህዝባዊ ወገንተኝነት ይገነባል፣ ይከራከራል፣ ሰላምን ይሰብካል። ከምንጨቃጨቅበት ይልቅ ያላስተዋልነው ግን የሚጠቅመን ትልቅ አጀንዳ አለን ብሎ ይሞግታል።

በአገራችን ለዘመናት ሲናፈቅ የነበረውንና አሁን ያለውን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ለማምጣት ሲሉ በጨለማው ዘመን የሞቱ አሉ።

እኒህ መስዋዕቶች ሳይማሩም ጭምር ልበ ብሩህ ነበሩ፤ የዚያን ጊዜውን ብቻ ሳይሆን የዛሬውን ተንብየው፤ ተዋድቀዋል። እንዳለትም የዛሬውን ህዝባዊ ስርዓት በሞታቸው

አውርሰውናል። እኒያ መስዋዕቶች እንደ ዛሬዎቹ ፅንፈኞች ግራና ቀኝ ሲሳሳቡ ስላልነበር፣ ሲገነባቡ አያቁሙም፣ ሲጨቃጨቁም አይጣሉም፤ መታረቂያቸው መርሃቸው ነው። መነሻቸውንና መድረሻቸውንም ያውቃሉ።

ሰይጣናዊው ጃዋር ሚንጫ ይዞ አጀንዳ በሚሰጥበት በዚህ ዘመን፣ አገሪቱ ከማንም በላይ የራሳችን መሆኗን ዘንግተን ለየትኛውም ጉዳይ ተከላካዩ መንግስት ብቻ እየመሰለን ሀሳብ በከፈለው ማዕበል ውስጥ ከአንደኛው ወግነን ወይም ለራሳችን ያደላን እየመሰለን ሌላውን በጥላቻ አይን የምናይ በየትኛውም መስፈርት ለሳላም አላዋጣንም። ከየትም የሚሰነዘረው ሃሳብ መነሻና መድረሻው የትም ይሁን መቋጫው ሰላማዊ መሆን አለበት፤ ያለንበትንና የምንኖርበትን ነባራዊ ሀቅና መድረሻችንን ያማለከ ትግል ማድረግም ይገባናል።

እንደ አገር መነሻችን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ነው፤ መድረሻችን ደግሞ ህዳሴና ብልፅግና ነው። ራሳችንን በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን በማየት ለመድረሻችን ከተጋን የጥፋት ሃሳብ ማረፊያ ስለሌለው አየር ላይ ይበናል። እንድንበላላ የሚሹት ጅቦችም ሊቀራመቱት የሚሹትን መሬት፣ የሚያቃቡትን ደም፣ የሚያባሉትን ማህበረሰብ ስለሚያጡ ከማላዘን በቀር አማራጭ አይኖራቸውም።
ታላቁ መሪ አቶ መለስ፣ “ውሾቹ መጮሃቸው ክፉ አይደለም፤ የመጮህ መብትም አላቸው፣ አለባቸውም፤ እንደ ቀድሞው መናከስ ግን አይችሉም፤ ምክንያቱም ጥርሳቸውን አውልቀንላቸዋል” ነው ያሉት? እርስ በእርስ ከመበላላት ሌላ አማራጭ ለሌላቸው ጅቦች ጠጠር ላለመሆን... የፅንፈኞችንም፣ የጠባቦችንም ትርጉም የለሽ አስተሳሰብ በያለበት መታገል ይኖርብናል።